የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፻፯
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፳፻፰ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 107
ADDIS ABABA, 8th September ,2016


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፰/፳፻፰ዓ.ም
ለጐሬ-ቴፒ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ………………………………………… ገጽ ፱ሺ፫፻፲


## CONTENT


Proclamation No. 978/2016
Export- Import Bank of Korea Loan Agreement for financing Gore-Tepi Road Improvement Project Ratification Proclamation ……..…………………..page 9310


### አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፰/፳፻፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለጐሬ-ቴፒ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፻፳፯ ሚሊዮን ፫፻፵፭ሺ የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ አርባ አምስት ሺ የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘውን የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሐምሌ ፲፱ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

### PROCLAMATION No. 978/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA**

**WHEREAS**, A Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export –Import Bank of Korea stipulating that Export-Import Bank of Korea amount of 127,345,000 USD (One Hundred and twenty Seven million Three hundred and forty five Thousand United States of Dollar) for financing Gore-Tepi Road Improvement Project was signed in Addis Ababa on the 26th day of May, 2016.

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 26th day of July, 2016 ;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለጐሬ-ቴፒ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፰/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **የ<u>ስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር ET-3 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፻፳፯ ሚሊዮን ፫፻፵፭ሺ የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ አርባ አምስት ሺ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the " Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing Gore-Tepi Road Improvement Project Ratification Proclamation No. 978/2016."

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number ET-3 signed in Addis Ababa on the 26th day of May 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export-Import Bank of Korea is hereby ratified.

3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 127,345,000 USD (One Hundred and Twenty seven Million Three Hundred and forty five Thousand United States Dollar) in accordance with the trems and Addition set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of September, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**